# መመርያ

## የሞንትጎመሪ ካውንቲ የትምህርት ቦርድ

**ተዛማጅ ምንጮች:** ABA፣ FFA-RA
**ኃላፊነት ያለው ጽ/ቤት:** የትምህርት ቤት ድጋፍ እና ደህንነት ዋና ኃላፊ ቢሮ
Office of the Chief of School Support and Well-being

## የትምህርት ተቋም ስያሜ

**A. ዓላማ**

የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ትምህርት ቤቶችን እና መገልገያዎችን የመሰየም የትምህርት ቦርድን ሃላፊነት መወሰን እና የትምህርት ቤት ስሞች የሚሰየሙበትን መመዘኛዎች ማስቀመጥ።

**B. ጉዳይ**

የህዝብ ንብረት የሆኑ ተቋማትን ወይም ትምህርት ቤትን መሰየም ማለት አርአያነት ያላቸው፣ ዋና እሴቶችን የሚያንፀባርቁ፣ እና በቦርድ ፖሊሲ ACA ላይ የተገለጹትን መርኆች፣አድሎ የሌለበት፣ ፍትኃዊነት/እኩልነት እና ባህላዊ ብቃት እንዲጎለብት የሞንትጎመሪ ካውንቲ ብዝሃነት በፍትሃዊነት እንዲንፀባረቅ ከፍተኛ ክብር እና ዝና በሚሰጣቸው ስም እንዲሰየም ማድረግ ነው።

**C. አቋም**

1. በቦርዱ ባለቤትነት ለተያዙ ት/ቤቶች እና ሥራ ለሚሠራባቸው ተቋማት ኦፊሴላዊ ስሞችን መሰየም የቦርዱ ኃላፊነት ነው።

2. በቦርዱ በግልጽ ካልተፈቀደና ካልጸደቀ በቀር የገንዘብ ጥቅም ለማስገኘት ተብሎ ት/ቤትን፣ ተቋምን ወይም የትምህርት ቤት ወይም የተቋምን በሙሉም ሆነ በከፊል ስም መሰየም የተከለከለ ነው።

3. የአንድን ትምህርት ቤት ወይም ፋሲሊቲ በከፊል መሰየም በቦርድ ፖሊሲ ABA መሠረት ከማህበረሰቡ የሚሰጠውን የአስተያየት ግብአት በጥንቃቄ ከመረመረ(ች) በኋላ፣ የማህበረሰብ ተሳትፎ፣እና ፖሊሲ ACA፣ መሠረት አድሎ የሌለበት፣ ፍትሃዊነት እና የባህል ብቃት በሠፈነበት አኳኋን መሆን አለበት።

4. ቦርዱ ትምህርት ቤቶችን እና መገልገያዎችን በመሰየም ላይ ያለውን ሀላፊነት በመወጣት የሚከተሉትን መደቦች እና ተስማሚ ስሞችን ለመምረጥ የሚያስችሉ መስፈርቶችን አዘጋጅቷል።

   a) የአሁን የቦርድ መርኆዎችን፣ ፖሊሲዎችን፣ ዋና እሴቶችን ወይም የትምህርት ዓላማዎችን የሚያረጋግጡ ሀሳቦች ወይም ጽንሰ-ሀሳቦች

   b) የሞንትጎመሪ ካውንቲ ጂኦግራፊያዊ ገፅታዎች

      1) ጂኦግራፊያዊ ስሞች በሰፊው እውቅና ሊኖራቸው ይገባል፣ እና

      2) ታሪክ በሠሩ ሰዎች ስም የተሰየሙ ጂኦግራፊያዊ ገጽታዎች ሰክሽን "section C.4.c." ላይ

የተዘረዘሩትን መስፈርቶች ማሟላት አለባቸው።

c) የሚከተሉትን መመዘኛዎች የሚያሟሉ ሰዎች ስም፡-

1) ሰውዬው ከዚህ ዓለም በሞት የተለየ(ች) መሆን አለበ(ባ)ት።

2) ሰውየው ለማህበረሰቡ፣ ለካውንቲው፣ለስቴቱ ወይም ለሀገሩ እና/ወይም የቦርድን እና የቦርድ ፖሊሲ ACA ዋና እሴቶችን ተምሳሌትነት ያሳየ(ች) መሆን አለበ(ባ)ት።

3) ቦርዱ የሞንትጎመሪ ካውንቲ ብዝሃነትን ለሚወክሉ እና/ወይም በፍትሃዊነት ላይ የላቀ አስተዋጽኦ ላደረጉ ሰዎች ጠንካራ ግምት ይሰጣል።

5. ውድቅ ሊሆኑ የሚችሉ የስም ምሳሌዎች የሚከተሉት ናቸው–

a) በፖሊሲ ACA ላይ እንደተገለጸው በግላዊ ሁኔታና ባህሪያት ምክንያት ሰዎችን ማዋረድ፣ማጉደፍ፣ማንኳሰስ፣ስም ማጥፋት፣

b) ነውር፣ ጸያፍ፣ ስድብ፣ በሀሰት ስም አጥፊ፣ማንቋሸሽ፣ንቀት ያደረበ(ባ)ት፣መረን፣ ባለጌ፣ ሀፍረተቢስ ወይም ሴሰኛ፣ ወይም ለማዋከብ፣ ለማስፈራራት ወይም ለዛቻ ዓላማ ያለው (ያላት)፣ አወንታዊ የትምህርት እና የስራ አካባቢን የሚያደፈርስ እና ከባቢ አየርን ለመጠበቅ ካለው ግብ ጋር የማይመጥን እና የጋራ መከባበርን የሚያጎድፍ ቋንቋ የሚጠቀሙ።

c) ከወንጀል ክስተቶች፣ ተግባራት ወይም ባህሪዎች ጋር ማዛመድ፣

d) የንግድ ወይም የንግድ ድርጅትን የሚመልከቱ፣ ወይም

e) ልቦለድ ገጸ-ባህሪያትን ይወክላሉ ወይም በቦርዱ ምክንያታዊ ክብር እንደጎደላቸው የሚገመቱ ቃላትን ወይም ሀረጎችን የያዙ ወይም ጎጂ፣ ወይም በሌላ መልኩ ልጆች ሊማሩት የማይገባቸው ለመግባባት ወይም ለሕዝብ እይታ እና ለዕድገት አግባብነት የሌላቸው ናቸው።

## D. የአተገባበር ስልቶች

1. ቦርዱ የትምህርት ቤት ወይም የመገልገያ ተቋማትን ስያሜ ዝርዝር አዘጋጅቶ ይይዛል እንዲሁም ለተጨማሪ ስያሜ ጥቆማዎችን ይቀበላል። ቦርዱ እንደዚህ ያሉ ስሞችን ከስያሜ መስፈርቶች እና ከቦርድ ፖሊሲዎች ጋር ለማጣጣም መደበኛ የሆነ ግምገማ ይቀበላል።

2. አዳዲስ ትምህርት ቤቶችን ወይም ተቋማትን መሰየም

a) አዲስ ትምህርት ቤት ወይም የተቋም ቦታ ሲገዛ ወይም ለአዲስ ትምህርት ቤት ወይም ተቋም ፕሮጀክት ዕቅድ ሲጀመር የት/ቤቶች ሱፐርኢንተንደንት/ተወካይ ቦታውን ወይም ሕንፃውን ለእቅዱ ዓላማ በጊዜያዊነት ስም ይሰይማል/ትሰይማለች።

b) አዲስ ትምህርት ቤት ወይም የፋሲሊቲ እቅድ ፕሮጀክት ሲጀመር ቦርዱ ከያዘው የስም ዝርዝር ውስጥ እስከ አራት የሚደርሱ ስሞችን ማህበረሰቡ እንዲመርጣቸው ያቀርባል።

c) የት/ቤቶች ሱፐርኢንተንደንት/ተወካይ በ "Policy ABA" የማህበረሰብ ተሳትፎን በሚመለከት የተቀመጠውን የማህበረሰብ ተሳትፎ ሂደት በመጠቀም የታሰበው አዲሱ ትምህርት ቤት በማህበረሰቡ ተንከባካቢነት ተማሪዎችን እና ወላጆችን በማገልገል ላይ ያተኮረ መሆኑን በመግለጽ

ከማህበረሰቡ ጋር በመመካከር እንዲሳተፉ ይደረጋል። የማህበረሰቡ ተሳትፎ አላማ በቦርዱ ከቀረቡት እስከ አራት ስሞች እና ከተሳታፊዎች የሚሰየሙ እስከ ሁለት ተጨማሪ ስሞች መካከል ቅድሚያ የሚሰጠውን የስም ዝርዝር መፍጠር ነው።

d) ቦርዱ የሚከተለው መረጃ ይሰጠዋል፡-

1) ስሙ C.2.c ላይ የተገለጹትን መመዘኛዎችን የሚያሟላ መሆኑን የሚያሳይ ትንታኔ

2) ስሙ የትምህርት ቤቱን ትምህርታዊ ተልእኮ እና ዓላማ እሴቶች ለማስፈጸም እንዴት እንደሚያገለግል

3) "Policy ABA" የማህበረሰብ ተሳትፎ ላይ በተገለጸው መሰረት የተከናወኑ የህዝብ ተሳትፎ እንቅስቃሴዎች ማጠቃለያ

e) ቦርዱ ከማህበረሰቡ ከተቀበለው ቅድሚያ ከተሰጠው ዝርዝር ውስጥ የትምህርት ቤት ስም ይመርጣል። ምንም እንኳን ቦርዱ ስለ ት/ቤት ወይም የትምህርት ተቋም ስያሜን በሚመለከት የማህበረሰብ ምክረሃሳቦችን የሚቀበል ቢሆንም፥ በጥንቃቄ ከታሰበበት በኋላ የትምህርት ቤት ህንጻ ወይም ተቋምን ስም በይፋ መሰየም የመጨረሻው ሃላፊነት የቦርዱ ኃላፊነት ነው።

3. ትምህርት ቤትን ወይም የመገልገያ ተቋምን ስም እንደገና መሰየም

a) ቦርዱ ነባር ትምህርት ቤትን ወይም ተቋማትን እንደገና ለመሰየም ከትምህርት ቤቱ ማህበረሰብ ተማሪዎች ወይም ከወላጆች/አሳዳጊዎች አቤቱታዎችን ይቀበላል። አቤቱታ በመቀበል ብቻ ቦርዱ የትምህርት ቤቱን ስም ለመቀየር ድምጽ አይሰጥም። አቤቱታውን ይገመግማል፣ እና የተገለጹትን መስፈርቶች የሚያሟላ ከሆነ፣ ቦርዱ ከዚህ በታች በተገለጸው መሰረት የማህበረሰብ ተሳትፎን ሊጠይቅ ይችላል።

1) ትምህርት ቤት/ተቋምን እንደገና ለመሰየም የሚቀርቡ አቤቱታዎች የሚከተሉትን መረጃዎች መያዝ አለባቸው፡-

(a) ነባሩ ስም በዚህ ፖሊሲ ውስጥ ተቀባይነት ካላቸው ስሞች መስፈርቶች ጋር እንዴት እንደማይጣጣም ወይም በሌላ መልኩ ስሙን "section C.4" ላይ ከተቀመጠው ምድብ እና መመዘኛዎች ጋር በሚያስማማ መልኩ የሚቀየርበትን ምክንያት የሚያሳይ ትንተና.

(b) ከተማሪዎች እና/ወይም ከትምህርት ቤቱ ማህበረሰብ ወላጆች/አሳዳጊዎች ቦርዱ በማህበረሰብ አውድ በሚወስነው መሰረት ከፍተኛ ድጋፍን የሚያሳይ አቤቱታ።

2) ቦርዱ ጠያቂዎቹ ሰክሽን D.3.a ላይ የተገለጹትን የሚፈልጉትን ክፍሎች እንዲያቀርቡ ከወሰነ፣ ቦርዱ በፖሊሲ ABA፣ የማህበረሰብ ተሳትፎ፣ ላይ - በተገለጸው መሰረት የት/ቤቶች ሱፐርኢንተንደንት የማህበረሰብ ተሳትፎ እንዲያካሂዱ ሊመራው ይችላል።

(1) አቤቱታ የቀረበውን የስም መቀየር ጥያቄ ለትምህርት ቤቱ ማህበረሰብ ማሳወቅ፣ እና

(2) ከተማሪዎች እና ከወላጆች/አሳዳጊዎች ጋር ስሙ ለአሁኑ የትምህርት ቤት ማህበረሰብ ስላለው ትርጉም እና በግለሰቦች ስም ለተሰየሙ ትምህርት ቤቶች፣ የግለሰቡ ህይወት የትምህርት ቤቱን ትምህርታዊ ተልዕኮ የሚያረጋግጥበት

ደረጃ፣ የትምህርት ቤቱ ማህበረሰብ እሴቶች፣ የቦርድ ዋና እሴቶች እና/ ወይም ፖሊሲ ACA።

3) እዚህኛው ደረጃ ላይ የሚደረገው የማህበረሰብ ተሳትፎ አላማ አዲስ ስሞችን ለመለየት አይደለም።

b) ቦርዱ የትምህርት ቤት ስሞችን እንደገና ለመገምገም በቂ የሆነ ገለልተኛ የታሪክ ትንታኔ ሊፈልግ ይችላል።

c) ትምህርት ቤቶች በስማቸው የተሰየሙላቸውን የግለሰቦች ህይወት ታሪክ እንደገና ሲገመግም ቦርዱ የሚከተሉትን ግምት ውስጥ ማስገባት አለበት፡-

(1) በግለሰቡ የሕይወት ተሞክሮ አውድ እና በቦርድ ዋና እሴቶችና በፖሊሲ ACA መካከል የታወቀ አለመግባባት/አለመጣጣም።

(2) ተቋማዊ እና ማህበረሰባዊ እሴቶችን ግለሰቡ በኖረበት ጊዜ እና አሁን ባለው ሁኔታ ከግለሰቡ ህይወት ወይም ትሩፋት ጋር ማመጣጠን ተገቢ ነው።

(a) ከግለሰቡ የሚወረስና ጉልህ አስተዋፅኦ እንዲሁም የግለሰቡን ህይወት፣ የህዝብ እና የግል ህይወት ሚዛን ግምት ውስጥ ማስገባት እና ነጠላ ድርጊቶችን ወይም ባህሪያትን ማግለል የለበትም።

(b) ወደ ተሐድሶ እና እርቅ ለመሸጋገር ያለፈውን ሁነት እውቅና መስጠት ግምት ውስጥ መግባት አለበት።

d) ቦርዱ ትንታኔው ት/ቤቱን ወይም ተቋሙን ከቦርድ ፖሊሲዎች ጋር ለማስማማት እንደገና መሰየም እንደሚያስፈልግ ከወሰነ፣ ቦርዱ የት/ቤቶች የበላይ ተቆጣጣሪ/ተወካዩ ከህብረተሰቡ ጋር የመመካከር አሠራር በመጠቀም ከላይ በሰክሽን D.2 እንደተገለጸው ለአዲስ ስም ስያሜ ቅድሚያ የሚሰጣቸውን የስም ዝርዝር እንዲያዘጋጁ ቦርዱ ወደ ት/ቤቶች የበላይ ተቆጣጣሪ/ተወካይ ይመራል።

e) የስም መቀየር ሂደት አካል በመሆኑ የሚያስከትለውን ወጪና ዋጋ ጭምር ቦርዱ ግምት ግምት ውስጥ እንዲያስገባ በት/ቤቶች ሱፐርኢንተንደንት/ተወካይ አማካኝነት ትንተና ማቅረብ ያስፈልጋል።

5. ትርፍ የቦርድ ንብረት የ MCPS ትምህርት ቤት ሆኖ እንዲያገለግል በድጋሚ ሲታቀድ ቦርዱ ያንን ተቋም እንደገና መሰየም ሊያስብበት ይችላል፣ በዚህ ጊዜ በሰክሽን D.2 እንደተገለጸው ስም ለመጠቆም የማህበረሰብ ተሳትፎ ይኖራል።

**E.** የትምህርት ቤቶች ሱፐርኢንተንደንት/ተወካይ ይህንን ፖሊሲ ለመተግበር የሚያስፈልጉ ደንቦችን እና መመሪያዎችን ይፋ ያደርጋል።

**F.** **ተፈላጊው ውጤት**

በቦርድ ባለቤትነት ስር ያሉ ትምህርት ቤቶችን ወይም መገልገያዎችን መሰየም እና ስም የመቀየር ሂደት እንደዚህ ያለ ከፍተኛ ክብር መስጠት ለህሳቦች፣ ለዋና እሴቶች እና የቦርድ ፖሊሲዎች በቦርድ ፖሊሲ ACA እንደተገለጸው አድሎ የሌለበት፣ እኩልነት እና የባህል ብቃት፣ እና የሞንትጎመሪ ካውንቲ ልዩነትን በፍትሃዊነት መቀበልን ይወክላል።

## G. *ግምገማ እና ሪፖርት*

ይህ ፖሊሲ በትምህርት ቦርድ የፖሊሲ ግምገማ ሂደት መሰረት ይገመገማል።

**የፖሊሲው ታሪክ፡-** የፀደቀበት ውሳኔ ቁ. 526-84፣ አክቶበር 9 ቀን 1984 ዓ.ም. (በውሳኔ ቁ. 333-86, ጁን 12 ቀን 1986, ክለሳ ተደርጎበታል፥ እንዲሁም በውሳኔ ቁጥር 458-86 ኦገስት 12 ቀን 1986) ተሻሽሏል፥ 419-90 ጁን 25 ቀን 1990 በውሳኔ ቁጥር 256-90፣ ተሻሽሏል፥ ኤፕሪል 17፣1990 (ከኤፕሪል 18፣ 1990 እስከ ኤፕሪል 17፣ 1994 (ስለ ትምህርት ቤት ስያሜ የመጀመርያውን የሚያብራራ/የሚሽር ፖሊሲ) የተሻሻለበት የውሳኔ ቁጥር 97-96 ፌብሩዋሪ 13 ቀን 1996፥ ተሻሽሏል። በውሳኔ ቁጥር 22-00, ጃኑዋሪ 11, 2000 ተሻሽሏል በውሳኔ ቁጥር 132-04, ፌብሩዋሪ 23 ቀን 2004 ተሻሽሏል፥ በውሳኔ ቁጥር 124-07 ማርች 13 ቀን 2007 ዓ.ም ተሻሽሏል፥ 285-22, ጁን 7, 2022. ተሻሽሏል።